በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 21-31 እና ፌብርዋሪ 1-10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 21/2024
አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

**እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ** ....- 1 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ....- 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት....- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 3 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 4 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ....- 5 -

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር....- 6 -

ሁኔታ ትንበያ ....- 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ....- 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 7 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ....- 7 -

ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 8 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ....- 8 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ....- 8 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ነበራቸው፡፡ በአጠቃላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአርባ ምንጭ 4.4፣1.8፣1.4፣5.0 እና 22.7፤ ሀዋሳ 0.5፤ ጎሬ 0.2፤ በጅማ 2.4፣3.1፣9.6፣19.3፣0.7 እና 2.7፤ በአዲስ አበባ 0.8 እና 1.0፤ በአምደወርቅ 31.4፤ በአምባ ማሪያም 4.2 እና 0.8፤ በአፅቢ 9.1፤ በአማን 10.6 እና 0.8፤በባቲ 3.1፤ በብላቴ 1.6፣1.7 እና 2.1፤ በቦሬ 50.6፣2.4 እና 4.0፤ በጭራ 15.6፣ በደብረወርቅ 4.7 እና 7.8፤በዲላ 28.8፤በዶሎመና 0.1፤ በእምድብር 1.8 እና 16.6፤ በእንዋሪ 4.0፤ በፍቼ 9.7፣2.6 እና 3.9፤ በጋቲራ 17.5 እና 0.7፤በጊዮን 18.0፤ በጉንዶመስቀል 2.3፤በቡሌ ሆራ 3.6፤ በጅንካ 7.0፣6.6፣0.5 እና 4.1፤ በኮንሶ 1.0፤ በላሊበላ 1.5፣0.7 እና 1.4፤ በሊሙገነት 9.1፤ በማጀቴ 2.7፤ በማጂ 0.5 እና 3.1፤ በማሻ 0.2፤ በመሃልሜዳ 4.8 እና 0.8፤ በምዕራብ አባያ 5.0፣7.0 እና 21.0፤ በሞጣ 0.1፤ በንፋስ መዉጫ 5.5 እና 16.9፤ በሳዉላ 28.0፣1.6 እና 15.2፤ በሰንቃጣ 7.2፤በሰኮሩ 1.8፤ በሻምቡ 0.1 እና 8.6፤ በሲርንቃ 0.9፤በወገልጤና 5.8 እና 0.5፤ በቴፒ 0.6 እና 8.3፤ በወላይታ ሶዶ 1.4 እና 2.5፤ በያቤሎ 18.8 እንዲሁም በተርጫ 1.2 እና 15.7 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

ባለፉት ጃንዋሪ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት ከሱማሌ ክልል አፍዴር፣ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከ10-56 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ 2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ጅማ፣ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፤ምስራቅ ወለጋ፤ሆሮ ጉዱሩ፤ምዕራብ ሸዋ፤ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ ሰሜን፣ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፤ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች ፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ እና አኙዋክ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ፣ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ፣ጉራጌ እና ስልጤ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከ1-35 በሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ባሌ፣ምዕራብ አርሲ፣ጅማ፣ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና እና ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞኖች፣የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ባስኬቶ፣ምዕራብ ኦሞ፣ጋሞ እና ጌደኦ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ማዕከላዊ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋግህምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ምስራቅ ጎጃም፣ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ዞን 2 እና 4 ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡


በሌላ በኩል የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ10 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ከ10 ዲ.ሴ በታች የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል ፡-





ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበር የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ የበጋ ወቅት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ የተስተዋለባቸው ቢሆንም፤ በመጨረሻዎቹ ቀናት በጥቂት የላይኛውና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በመካከለኛውና በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦ እና ተከዜ እንዲሁም አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ እንዲሁም በጥቂት መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ እና በላይኛው ገናሌ ዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አባይ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ እና ኦጋዴን፣ የበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ የመጨረሻ አሥራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚቀጥልበት ነው፡፡

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7፡፡ በሌላ በኩል የሰሜን፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ይኖረዋል( ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ የጉጂና የቦረና ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣ ዞን 4 እና ዞን 5፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ የሊበን እና የአፍዴር ዞኖች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም በጥቂት የሀገራችን አከባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ( ካርታ 6)፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በመደበኛ ሁኔታ በፌብሪዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍልች ላይ ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍልች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂና ቦረና ዞኖች፣ የምዕራብና የምስራቅ ሐረርጌ፤ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን እና ኖጎብ ዞኖች፤ እንዲሁም የሐረሪ እና ድሬዳዋ ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3 ና 5፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ ዞን ቀላል ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 8) ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 1-10 Feb 2024




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛውና የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትም ሆነ ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የሚኖረው እርጥበት የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት እና ዘር ለመዝራት የሚያስችል በመሆኑ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣዮቹ ቀናት በላይኛውና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አሞ ጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ የመካከለኛውና ምስራቃዊ አባይ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ ገናሌዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡